# <u>ከቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የሰሜን አሜሪካ የልኡካን ቡድን የተሰጠ መግለጫ</u>

**ጥቅምት 7 ቀን፣ 2000 ዓ.ም**
**ዋሽንግተን ዲ ሲ**

የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ ልኡካን ቡድን ከኢትዮጵያ ከመነሳቱ በፊት ጀምሮ፤ አሜሪካ ከገባም በኋላ እስካሁን ድረስ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል በሊቀመንበርነታቸው ቡድኑን እንዲመሩና የቡድኑ አባላትም የተሰጣቸውን ተልእኮ በጋራ እንዲወጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲጠይቃቸው ቆይቶአል:: እሳቸው ግን የቡድኑን ጥሪ እስካሁን አልተቀበሉትም:: ስለዚህ የቡድኑን ተልእኮ ከተቀሩት የቡድኑ አባላት ጋር በመሆን እያስፈጸሙ አይደሉም:: ከዚያም አልፈው በአሁኑ ጊዜ የራሳቸውን አጀንዳ አውጥተው በቅንጅት ስም ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው:: ተግባራዊ የሚያደርጉትም የሚመለከታቸው የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት አባላት መክረው ባፈረሱትና ኢንጅነር ሀይሉ ሻውልም መፍረሱን በፊርማቸው ባረጋገጡት ራሱን «የቅንጅት አለም አቀፍ ምክር ቤት» ብሎ በሚጠራና በቅንጅት ባልታወቀ አካል አማካይነት ነው:: በተጨማሪም ጉዳዩ ከሚመለከተው የላእላይ ምክር ቤት አካል ውሳኔ ውጪ የምክር ቤት አባል የሆኑም ያልሆኑም ሰዎችን በራሳቸው ፈቃድ እያስመጡ በቡድናቸው ውስጥ በአባልነት እንዲንቀሳቀሱ እያደረጉ ነው::

በቅንጅት የልኡካን ቡድን ውስጥ የሚታየው ጊዚያዊ ችግር እንደሚባለው በግለሰቦች መካከል በሚካሄድ የስልጣን ሽኩቻ ምክንያት የተፈጠረ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀትንና የጋራ አመራር ስርአትን በመቀበልና ባለመቀበል መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የተፈጠረ ሁኔታ ነው:: ይህንንም ቅንጅት በአለው ሕገ ደንብ መሠረት ጉዳዩን በሀገር ውስጥ በዝርዝርና በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል:: እስከዚያ ድረስ ግን የልኡካን ቡድኑ የተሰጠውን ተልእኮ በአግባቡ ለማጠናቀቅ ማድረግ ያለበትን ማከናወኑን ይቀጥላል::